# ግጥም በየዓይነቱ

በዘውገ ፋንታ
ስያትል 2009

ደርሷል የሱ ተራ
ቀኑ በሱ ፋንታ
ባላባት አደራ፣
ሀገር ሕዝብ ሲፈታ።

ተጓዘ ሰው ወጣ
ሄደ በጋጋታ
ደስታ ቢያጣ፣
ወተት በገበታ፣
ሲኖር እየጠጣ፣
ይህ ሆኖ እፎይታ፣
ስጋ እንደቂጣ፣
ቋንጣ ቢታጣ

ሳናውቅ ሰፊ ዱሩን
ተኩላ በላ አንበሳ
በጨለማ እየሄድን
ፍለጋ ያን ካሳ
በቀን እየተኛን
ሰው እንዴት ይረሳ
መሪ ሳያቅተን
መገልበጥ ሬሳ።

ጠጋ ወዴት ጠጋ
ቀረብ ወዴት ቀረብ
ዘውድ የለሽ አልጋ
ምን ተገኘ ስበብ
ቀብሮ ፍለጋ
ከቶ ያንቺ መዝገብ
እንዴት ይነበብ?

አንቺ የኛ ንግሥት
አታውቂ ቀለሙን
አደረጉሽ ዮዲት
አሳጣሺው ክብሩን
አቆሸሺው ቅርሱን።

ጥበብ ነው ሲበቅል
ጥፋት ሲረግፍ
እሱ ያንቺ ኃይል
ይኼ የኛ ዛፍ
ሲጥሉት ይቆማል
እምቢ እያለ አላልፍ።

በውሃ ሲጫዎት
ቁልቁል አርጎ ቤቱን
አጣ እርጥብ መሬት
አድርቆ የራሱን።

ፎቀቅ ወዴት ፎቀቅ
ከሱ ከኛ ዘመድ
ማን ይስማ ማን ይወቅ
ይኼን ያንቺን መንገድ
እየጠሉ መውደድ።

ሁሉም ባማረ
መሬቱ ባልሰፋ
ተራብቶ በኖረ
ሲሄድ ከሚጠፋ።

አትበሉ ይኮብልል
ይኑር ከጠባቡ
እያለ፡ "መቻቻል!"
አይፍቱ ይጋቡ።

ሲኖር እንደልቡ
ተገዶ መች ያውቃል
ወጥሮ በስበቡ
አሁን ይናፍቃል
ተረዳው ልቡ
ካገር ምን ይልቃል።

ሸቅጦ ኪሳራ
የዘንድሮው ንግድ
አምልጦ መከራ
ምን ይበል ያትውልድ?
ነገ የሚወለድ።

ባይሰጡት መውጫ
ይሻል ነበር አሉ
ባለበት ቢንጫጫ
ሁሉም እንዳመሉ
በቀረ ሩጫ
መራመድ ካልቻሉ።

ይ.መለስ ደግ ይግባ
ካሳሩ ቤታችን
ሁሉም አይጠላ
ነውና ጎናችን
ከወጣ በመላ
ሌላው ጠላታችን።

የሞተው ይቆጠር
ሰባ ዕልፍ አድርጉት
እሺ ካለ አይኑር
ቀሚስ አታልብሱት
እምቢ ካለ ይብረር
በጣይቱ ሞት
ያሱሪ ይከበር።

መለኪያውን ይስጠን
ጣይቱን ወይ ካሳ
ይ.መለስ ያቀን.ቅን
የተኛው ቢነሳ።

በቀለም ያበድከው
ማን አሉት ስምህን?
እስቲ እንወቀው
ተግባር መላህን።

ሁለመናህ ልውጥ
ግጭት መደብርህ
እኛ አልንህ "ፍሬ.ሩጥ"
በለመድከው ይጥሩህ።

አያድርስ አይጣል
በቋንቋ ተጣሉ
ያስማማችሁ ቢባል
አማር.እኛ አሉ
ባቢሎን ይሆናል
ጦብያን ከበደሉ
አይቀርም ለሁሉ።

ፍሬው ተለቀመ
ሦስት ሺ ይፍረደው
ጣና አልተጠቀመ
እሱ አምላክ ይርዳው
በሽር ልጅ ከሰመ
መርቶ ካልመለሰው።

ቅናት የገደለው
ባንዳ.አንድ ተሾመ
ሠለሞን ዘር ጠፋው
ለንደን ተሰየመ
ይነሳ የሮሃው
አክሱም ከበቃው።

በለንደን ፈለቀ
ሳይጠፉ ዘራችን
ስንወድቅ አለቀ
ጆርጅ ሆነ አያታችን
ዓለም ተደነቀ
ተደፉ ደማችን
ሱባን ካላወቀ
ሰማንያ ቋንቋችን
ብዙ ነው ዘርፋችን።

ይ.መለስ የዘንዶው
ኮከቡ ካለፈ
ተፈሪ ያንበሳው
ለማን ተላለፈ?

ይኼ ነበር መላው
የቅርቡ የሩቁ
ምን አለ አገው
ወርቅ ሲሄድ ዕንቁ?

ይቅርብኝ ያዘር
ከሷ ካልበቀለ
ተኮትኩቶ ከስር
ኢጦብያ እያለ።

አይፍሰስ የኛ ደም
አጥንት አይሰበር
በዚህ በኛ ዓለም
እኛን ጥሎ አፈር
ሸቀጡን አናውቅም
የኛ ልብ ባህር
አየ የሱ ነገር
ሰው አለ ብር.ብር።

ትንሿ መዘክር
ትልቋ ሀብታም
እሷን ነው መዳር
እንዲገኝ ሠላም
ሳይበላሽ መንደር
አትበሉ ጭጭ ዝም
ወንድ ሳያልቅ ባላገር
እሷን የሚደፍር
ሕግ የሚሰብር!